SEP
2020

Monthly Newsletter Vol 17 No.1

፳፻፲፫
2020/21
2013



# መልካም አዲስ ዓመት



ECSU Graduates Students

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ



ኢሲሰዩ የ10 አመት ስትራቴጂክ እቅዱን አጸደቀ

CUDE holds proposal validation work shop



## ራዕያችን

የሀገራችንን ልማትና ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ግልጽና ተጠያቂነት ያለው ፐብሊክ ሰርቪስ ከመገንባት አኳያ በ 2017 በአፍሪካ የልህቀት ማዕከል መሆን

## ተልዕኳችን

ፐብሊክ ሰርቪሱ የአገልጋይነት መንፈስ የተላበሰ እና በግልጽነትና በተጠያቂነት የሚሰራ እንዲሆን አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣በስልጠና፣ በማማከር፣በምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶቻችን

ተገልጋይ ተኮር
ቁርጠኝነት
ሁሌም መማር
ብዝሀነት መቀበል
ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ
አሳታፊነት
ተባብሮ መስራት

## Our Vision

To become a leading center of excellence in public service capacity building in Africa by 2025 through building efficient, effective, Transparent and accountable public service which can contribute to the realization of the development and transformation drive of the country

## Our Mission

Enhancing the service orientation, transparency and accountability of the public service by building its capacity through Specialized Education,Training, Consultancy, Research and Community Services.

## Our Values

Customer Focus
Commitment
Continuous Learning
Welcoming Diversity
Attention to the Disadvantaged
Participation
Collaboration

# Ethiopian Civil Service University

## Content


ECSU GRADUATES STUDENTS 1

ECSU DONATES FOOD STUFF 3

CUDE HOLDS PROPOSAL VALIDATION WORK SHOP 4

የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ የአስር አመት መሪ አቅድ ላይ ውይይት ተካሔደ 5

ኢሲሰዩ የ10 አመት የተቋሙን ስትራቴጂክ እቅድ አጸደቀ 5

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የ2012ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ቅኝት 8



Editor In -Chife
Wondimu Moges

Editors
Wondimu Moges
Tariku Ayano
Anteneh Demisse

Photos
Ibsa Bekele
Dereje Tesfaye

Grafix Design
Dereje Tesfaye


## የዝግጅት ክፍሉ መልእክት

እቅዳችንን ወደተግባር ለመለወጥ በጋራ በመተሳሰብ መንፈስ በመስራት ሀገራችን ወደምትጓዘዉ የለዉጥ ሂደት ሁላችንም የየድርሻችንን እናበርክት ፡፡ እዉቀት ክህሎት  እና ስነምግባር ያለዉ ሲቪል ሰርቫንትን ለመፍጠር ሁላችንም የየድርሻችንን እንወጣ ፡፡አዲሱ አመት እቅዳችንን በአግባቡ የምንከዉንበት አና እቅድ ከዉጤት ጋር አስተሳስረን የምንሄድበት አመት እንዲሆልን እንመኛለን፡፡

ውድ አንባቢያን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ ህንጻ ቁጥር5 ቢሮ ቁጥር 210 ድረስ በአካል በመምጣት ወይም በኢሜል pr.ecsu@gmail.com  አድራሻችን በመላክ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡በተጨማሪ የኤሌክትሮኒክስ ወርሃዊ ህትመታችንን በ ድህረገጻችን (www.ecsu.edu.et) GALLERY (Megazine and Newsletter) በሚለዉ ስር ታገኛላቹ  ፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ECSU GRADUATES STUDENTS

Ethiopian Civil Service University graduated 2000 students with Masters and Doctoral Degrees, with virtually held commencement on Saturday, 15 August 2020.



Dr. Lemma Gudissa, Academic Vice President, on the occasion congratulated the graduates and all the university community for their biggest achievement. This year`s graduation is different from our graduation held in the past years due to



a threat caused by COVID-19, he said. 'Considering the global widespread of Corona pandemic, the University has taken so many measures; first by suspending the face-to-face education, students are sent to their home by delivering transport up to the capital cities of regions. We applied different technological platforms to facilitate the teaching-learning process. The thesis defense was also held virtually to our satisfaction. Besides the university delivered quarantine services for more than 1110 persons under investigation.



**Dr. Lemma Gudissa**
*Academic Vice President of ECSU*

For the candidates who could not graduate due to various reasons, the university will facilitate everything to continue from where they stop. So he urged them to be patient and wait until we solve the situation,he underscored.

He also conveyed his message to the graduates to apply the knowledge and skills they acquired during their stay at the university and deliver the service diligently and assist the national transformation process.

Dr. Lemma Gudissa finally said, 'I thanked the university management and university community who work hard and make this graduation real. Surely we will get out of this pandemic and work together with great determination to develop our country.





**Abdu Muhammed (Ph.D.)**
*Registrar and Alumni Directorate Director*



**Bisrat Kifle(Ph.D.)**
*Vice Dean, CUDE Environmental Management*



**Tesfaye Abate (Ph.D.)**
*Dean, College of Leadership and Governance*



**Lemessa Bayissa (PhD)**
*Dean, College of Finance, Management and Development*

























# ECSU Donates Food Stuff

In Response to "National Food Sharing Campaign'' ECSU has donated foodstuff to the nearby woreda 11and 9 from Yeka and Bole sub cities respectively with low incomes and elderly people on Saturday, August 15, 2020



ECSU president, Professor Fikre Dessalegne, handed over the donation to the needs in a ceremony held at the main campus of the university. He said ECSU has played its role in building the capacity of the public servants for the last 25 years. This time considering the effect of the epidemic, we have contributed our small support and be part of the "National Food Sharing Campaign'' stated at the national level. We know this is not enough but at least we share the burden of our communities who are elder and low income he underscored.



"I am honored to be part of this National Food Sharing Campaign and helping elderly people and those who need it most. We continue our responsibilities and work together to mitigate the impact of COVID-19," the president added.



**Professor Fikre Dessalegn**
*Ethiopian Civil Service University President*

The woreda 11 and 9 representatives on their part thanked the ECSU community for the donation and asked the university to continue such aid and play its responsibility.



The food supplies distributed to 300 elderly and needy people selected from worda11 and 9 in the tow sub-cities who were particularly vulnerable to the pandemic .For individual person, 25 kg flour and 5-liter palm oil were distributed.



# College of Urban Development and Engineering holds proposal validation work shop

Ethiopian Civil Service University Research and Community Service under College of Urban Development and Engineering held proposal validation work shop on trajectories of Urbanization and Urban Transformation in Selected Lakeside Cities of Ethiopia: Lessons and Future Directions (The Case of Bahir Dar, Hawassa, Arbaminch,Bishoftu,Haik and Ziway Towns) on August 19,2020 at Hidasse Hall.



**Dr. Daniel lirebo**
*Dean of College of Urban Development and Engineering*

Dr. Daniel lirebo, Dean of College of Urban Development and Engineering, welcomed the participant. He said the agenda of the Seminar covered issues associated with the basic themes of trajectories of Urbanizations. So we request participants to contribute ideas, comments to enrich this proposal successful .Surly, this validation workshop could provide the improvement for better proposal enrichments. "As a university community, we must join in an action-oriented effort to attack and solve the problems that beset Urbanization and its Management "he underlined.



Dr. Belewu Dagnew, Deputy Dean of Research and Community Service under College of Urban Development and Engineering, said ECSU is undertaking a wide research aimed at strategies that would enable to successfully manage the transformation of lakeside cities that is engaged by the fast rate of urbanization. So we will give every support to make such research practical and add knowledge and contribute our share for police makers as a higher education center. Besides the university enable students see practical aspects of the theoretical research ideas he underscored.

Proposals on Demographic and Spatial Growth Trends and Dynamics in Lakeside Cities, Lake Degradation and Environmental Infrastructure, Private Investment and their Impact on Livelihoods and Access to Public Spaces in Lakefront Areas, Inclusive and Participatory Planning in Lake Front Areas, Financial Distribution of the Thematic Area and Conclusion were presented respectively.



**Dr. Belewu Dagnew**
*Deputy Dean of Research and Community Service under DUDE*

Finally the participants raised different issues and forwarded their comments in each proposal to incorporate in the final draft.

# የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ የአስር አመት መሪ አቅድ ላይ ውይይት ተካሔደ

የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ የአስር አመት መሪ አቅድ ላይ ከተጠሪ ተቋማቱ አመራሮች ጋር ውይይት አካሄደ።

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ በዛብህ ገብረየስ ውይይቱን አስመልክተው እንደገለጹት በመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ ባለፈው አመት በርካታ ተግባራት የተከናወኑ መሆኑን ገልጸው የመንግሥት አገልግሎት ዘርፍ የአስር አመት መሪ አቅድ ነጻ፤ ገለልተኛና ብቃት ያለው አገልጋይ መፍጠር ላይ ማእከል ያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።



በመቀጠልም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የ10 አመት መሪ እቅድ፤ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፤ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፤ የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢኒስቲትዩት፤ የኢትዮጵያ ከይዘን ኢኒስቲትዩት እና የመለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ የ2012 ዓ.ም አፈጻጸም፤ የቀጣይ የአስር አመት መሪ እቅድና የ2013 አመታዊ ዕቅድን በተከታታይ አቅርበው ውይይት አድርገዋል።

ውይይቱም ነሀሴ 13 እና 14 ቀን 2012 ዓ.ም ለሁለት ተከታታይ ቀናት ተካሄዷል ።

ምንጭ ፡ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

# ኢሲሰዩ የ10 አመት ስትራቴጂክ እቅዱን አጸደቀ

የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ከ 2013-2023 የሚቆይ የ 10 አመት ስትራቴጂክ እቅድ ያቀደ ሲሆን በእቅዱም የተለያዩ ሁነታዊ ዳሰሳዎችን በማካሄድ19/12/ በ2012 ለየዘርፍ ሀላፊዎች ርክክብ አድርገዋል።

በርክክቡ ወቅት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጠቅላላ የስትራቴጂክ እቅድ ሂደቱን ሲያብራሩ ይህ እቅድ በተለይ ሀገራችን ባጋጠማት ወረርሽኝና በተለያዩ ሂደቶች በታቀደለት ግዜ ያልተጠናቀቀ ሲሆን ነገር ግን ባደረግነዉ ርብርብ በተለይ የእቅዱ ኮሚቴ አባሎች ባሳዩት ቁርጠኝነት ለዛሬዉ ፍጻሜ ደርሶአል ብለዋል። ለዚህም ያለኝን አድናቆት ለኮሚቴዉ አባሎች መግለጽ እወዳለዉ በማለት ገልጸዋል።



በማስከተልም ፕሮፌሰር ፍቅሬ ሲያብራሩ ባለፉት 25 አመታት በዋናነት በተለይ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም በትምህርት፣በስልጠና፣በማማከርና ማህበረሰብ አግልግሎት ስንገነባ ቆይተናል በዚህም ከፍተኛ ዉጤት አስመዝግበናል። አሁን ደግሞ ባለፉት ጊዚያቶች ስንሰራዉ የነበረዉን ተግባር ከጥራትናከተደራሽነት አንጻር ትልቅ ትኩረት በመስጠት በቁርጠኝነት እንሰራለን ።በተለይ በዋናነት ወጣቱ ሲቪል ሰርቫንት ሀገር ወዳድ፣የይገባኛልናየኔነት ስሜት ያለዉ/ያላት እንዲሆኑ የሞራል ግንባታ ላይ የ10 አመት ስትራቴጂክ እቅዳችን ከያዛቸዉ አንዱ ና ዋንኛዉ ጉዳይ ነዉ። ይህ እንግዲህ የሚሳየን በትምህር ብቻ ሳይሆን በሞራል ግንባታ ላይ ካልሰራን ብዙ ለዉጥ እንደማይመጣ ያየነወ ጉዳይ ስለሆነ ነዉ። በዚህም በሚቀጥሉት አመታት በወጣት ሲቪል ሰርቫንት የአቅም ግንባታ ላይ ትልቅ ስራ እንሰራለን ።



**ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ**
የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት



**ዶ/ር ለማ ጉዲሳ**
የአካዳሚክ ም/ፕሬዚዳንት

በሁለኛ ደረጃ የሲቪል ሰርቫንቱን ብቃት ከማረጋገጥ አንጻር ትልቅ ስራ እንደምንሰራ በእቅዳችን አመላክተናል ለተግባሩም የየድርሻችንን እንወስዳለን ። ከትምህርት ተቋም ተመርቆ ቀጥታ ስራ መቀጠል ሳይሆን ሲቪል ሰርቫንቱ እራሱን የሚያበቃበት ፣አዳዲስ አሰራርና ግኝት ጋር የሚላመድበት አለም በደረሰበት ደረጃ አቅም ያለዉ ሲቪል ሰርቫንት ከመፍጠር አንጻር ትልቅ ስራ እንሰራለን። ይህ ደግሞ በየግዜዉ የሲቪል ሰርቫንቱ ብቃት መረጋገጥ ስላለበት ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሆን የምንሰራዉ ስራ ይሆናል ።

በማስከተል ሲያብራሩ ማንኛዉም ስራ በቡድን መንፈስ ከልተሰራ ወደ ዉጤት መቀየር እንደማይቻልና የበለጠ አቅማችንን በማጎልበት በሙሉ ሀይል ከሰራን ዉጤታማ መሆን እንደሚቻል ለዚህም ማሳያ የስትራቴጂክ እቅድ የኮሚቴ አባሎች ያላቸዉን የቡድን መንፈስ በማድነቅ ለዉጤታማ ስራ በጋራና በኔነት ስሜት ማቀድ፣መተግበር ወሳኝ እንደሆነ አብራርተዋል። ስለዚህ ሁሉም የተቋሙ ሰራተኞች ይህን ማዳበር እንዳለበቸዉና የእቅዱ ዉጤታማነት የሚለካዉ በተጨባጭ የየዘርፉ አመራሮች ወደታች በታቀደለት ሂደት ሲያወርዱት እንደሆነ ገልጸዋል።



**አቶ ገብረትንሰዬ ተስፋይ**
የኮሚቴዉ ሰብሰቢ





**የ10 አመት ስትራቴጂክ እቅድ ኮሚቴ አባላት**



በስተመጨረሻ አበክረዉ የተናገሩት ይህ የ 10 አመት ስትራቴጂክ አቅድ የዩንቨርሲቲዉን ተልእኮ ወደላቀ ጉዞ የሚያስኬድ ሲሆን ነገር ግን ለትግበራዉ ሁሉም የተቋሙ ማህበረሰብ የዉስጥም የዉጭም ባለድርሻ አካላት የየራሳቸዉን ሚና መጫወት አለባቸዉ። ተግባር ከሀላፊነት ጋር ከተጠያቂነት ጭምር ወደታች መዉረድ ያለበት ሲሆን ለዚህም በተለይ የቁጥጥርና ግምገማ ሂደት በየጊዜዉ መካሄድ፣ ክፍተቶችን በመለየትና በማስተካከል  በየደረጃዉ ያሉ አመራሮች ሀላፊነታቸዉን  መወጣት አለባቸዉ ብለዋል።



የኮሚቴዉ ሰብሰቢ የነበሩት አቶ ገብረትንሰዔ ተስፋይ የከተማ ልማትና ትራነስፎርሜሽን ስልጠናና ማመከር ማእከል ዳይሬክተር ሲያብራሩ ለዚህ ስኬት በዋናነት የአመራሩ ቁርጠኝነት በማድነቅ በሂደቱ ያጋጠሙዋቸዉን እክሎች በዉይይት እንዴት እንደፈቷቸዉ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ሲያብራሩ እቅዱ ሁሉንም ዘርፎች ያሳተፈ በተጨባጭ ብዙ የተሰራበት የተለያዩ አካላት ማለትም ለከፍተኛ አመራሩ ፣ለቦርድ አባላት ለ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ  አስተያየት ተሰጥቶበት አስተያየቱ ዳብሮ የተካተተበት እንደሆነና የኮሚቴዉ አባላት ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት አድንቀዉ በተለይ ይህ እቅድ በደንብ ወደ ፈጻሚዉ ዘንድ እንዲወርድ ያላሰለሰ ጥረት እንደሚደረግ፤ ማቀድ ብቻ ሳይሆን በማስረጽ ሂደትም የየራሳቸዉን ድርሻ እንወጣለን በማለት ነገርግን ትልቁና አብይ ስራዉ ሁሉም የየዘርፍ አመራሮች ወደ ተግባር እንዲለወጥ በማስፈጸም ሂደት ላይ  በጥንካሬ መስራት አለባቸዉ ብለዋል።



የዩንቨርስቲዉ   የአካዳሚክ ም/ፕ ዶ/ር ለማ ጉዲሳ በበኩላቸዉ ዩንቨርስቲዉ በተለይ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚደግፎ በአደረጃጀትና በግብአት ዙሪያ እየሰራ ያለዉን ሂደት አብራርተዋል ፡ ፡በተለይ በአሁኑ ወቅት በመጠናቀቅ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች  ለመማር ማስተማሩ ያለቸዉን አስተዋጽኦ ገልጸዋል።  በመጠናቀቅ ላይ ያሉ ግንባታዎች የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ ያላቸዉን ጥቅም በዝርዝር ገልጸዋል።





# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የ2012ዓ.ም የስራ አፈጻጸም ቅኝት

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም ለመገንባታ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት በጥናት ላይ የተመሰረቱና አግባብነት ያላቸውን የቅድመና የድህረ-ምረቃ ስፔሻላይዝድ የትምህርት ፕሮግራሞች ቀርጾ በማስተማር፣ አጫጭርና ተከታታይነት ያላቸውን ስልጠናዎችን በመስጠት የመንግስት ሰራተኞችን፣ የእውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ክፍተቶች ለመሙላት እየሰራ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪ በፐብሊክ ሰርቪሱ አደረጃጀት፣አሰራርና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማካሄድና የማማከር አገልግሎት በመስጠት፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ተቋማት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ከማስቻል አንጻር ግንባር ቀደም ሚና እየተወጣ ይገኛል።

ዩኒቨርስቲው ይህንኑ ኃላፊነቱን በተጠናከረ መልኩ ለመወጣት እንዲችል በተዘጋጀው የአምስት ዓመቱ (2008-2012) ስትራቴጂክ ዕቅድና ከ2011 በጀት ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ በመነሳት ለ2012 በጀት ዓመት 9 ግቦችን በመለየትና ግቦቹን በአራቱ እይታ በማስቀመጥ የ2012 የውጤት ተኮር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል። የዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ሪፖርት እንደሚያመለክተውም የዕቅዱ አፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱ እየቀረበ ግምገማና ክትትል ሲደረግለት ቆይቷል። ከቀረበው የማጠቃለያ ሪፖርት ለመረዳት እንደሚቻለው በ2012 በጀት ዓመት አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በሚሰጣቸው አገልግሎቶች የተገልጋዮችና የባለ ድርሻ አካላት የእርካታ ደረጃ በተሟላ መልኩ ለመለካት በሀገራችን በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ አዳጋች አድርጎታል። ነገር ግን በዩኒቨርሲቲው በተሰጡ ስልጠናዎች እና በስልጠናና ፋሲሊቲና መስተንግዶ አገልገሎቶችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው በሚሰጡ ስልጠናዎች ላይ የሰልጣኞች ዕርካታ 95.3% እንዲሁም ለፐብሊክ ሰርቪስ ተቋማት ዩኒቨርሲቲው ለሰልጣኞች በሰጠው የሥልጠና ፋሲሊቲና መስተንግዶ አገልግሎት 95% ፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ደግሞ 94.5% የእርካታ መጠን ተመዝግቧል።

ከፋይናንስ ዕይታ አንጻር የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሻሻልም የጥሬ ገንዘብ ቆጣራ ሪፖርት በየወሩ ለማዘጋጀት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን የ2011ዓ.ም የበጀት አጠቃቀም ሪፖርትና የ2012 በጀት ዓመት የፕሮግራም በጀት መርሐ ግብር እንዲሁም ከ2013- 2015 ድረስ ያለውን የ3 ዓመት የፕሮግራም በጀት ጥያቄ ተዘጋጅቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ተልኳል። የዩኒቨርሲቲው የሀብት አጠቃቀም የመንግስት የፋይናንስ አሰራር ተከትሎ መፈጸሙ በኦዲት የተረጋገጠ ሲሆን በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኦዲት ግኝቶች የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የተጠየቁ የማስተካከያ እርምጃዎች ተወስደው ሪፖርት ተደርጓል። በIFMIS ሥርዓት የበጀት አጠቃቀምን በመከታተል ወቅታዊ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ቀርቧል። በጠቅላላው ከተፈቀደው በጀት (ለግንባታ እና ለምርምር በተሰብሳቢ የተከፈለ ሳይጨምር)ከብር 556,596,534.97 ውስጥ ብር 522,711,940.01 (94%) በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

የንብረት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓትን ለማሻሻልም በIFMIS ስርዓት የንብረት ምዝገባ በማካሄድ ንብረቶች በተዘረጋው ስርአት መሰረት ገቢና ወጪ እየተደረጉ ይገኛል:: በቤተመፃህፍት ለ10 ዓመት ያልተካሄደ የኢንቨንተሪ የተካሄደ ሲሆን በካይዘን ትግበራም ግምታቸው ብር 181,809 የሚሆኑ ንብረቶች ለቤተ መጽሀፍቱ የማያስፈልጉና ለሌሎች ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ንበረቶች ተለይተዋል። በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት የካይዘን ትግበራው ከመጀመሪያው ትግበራ ወደ ቀጣይ ትግበራ ተሸጋግሯል። በኔትዎርክ ዝርጋታ፣ በጥገናና በንብረት አያያዝ ግምት ብር 800 ሺህ ተቆጥቧል። አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በህግና በደንቡ መሠረት ተወግደው ብር 528,655 ገቢ ተደርጓል። የገቢ ምንጮችን ማስፋፋትና ገቢን ለማሳደግ በታቀደው መሰረትም ከፕሮጀክት ስምምነቶች፣ ከተማሪዎች መመዝገቢያና የትምህርት ክፍያ፣ ከቅጥር ፈተና አገልግሎት፣ ከስልጠና፤ ማማከር፣ ፋሲሊቲ አገልግሎቶች፣ ከኮምፒዩተር ላብራቶሪና ኢንተርኔት አገልግሎት እና ከህትመት አገልግሎት ብር 62,200,000 ለመሰብሰብ ታቅዶ ያልተጣራ ከዕቅድ በላይ ብር 82,887,357.23 (133.30%) ተሰብስቧል ።

የዩኒቨርሲቲውን አገልግሎቶች አግባብነት፣ ጥራትና ተደራሽነት ለማሳደግና ተቋማዊ ገጽታ ግንባታን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው

ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ 20 ህትመቶች የተሰራጩ ሲሆን 18 አጫጭር የቪዲዮ ዜና ዘገባዎች ለመስራት ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 19 ማከናወን ተችሏል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ድረ-ገጽ ወቅታዊ የማድረግ ሥራ በማከናወን ወቅታዊ እንቅስቃሴዎች በድረ-ገጹ አማካኝነት ተሰራጭቷል፡፡ ከኮተቤ ሜትሮፖሎቲያን ዩኒቨርሲቲ፣ ከአዲግራት ዩኒቨርሲቲ፣ ከመቱ ዩኒቨርሲቲ እና ከጂማ ዩኒቨርሲቲ ለመጡ ተወካዮች ስለዩኒቨርሲቲያችን እንቅስቃሴ የልምድ ተሞክሮ ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናና ማማከር ዘርፍ የሚከናወኑ አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ በዩንቨርሲቲው በዌብሳይት አዳዲስ ብሮሸሮች እና 99 የስልጠና ርዕሶች በአመታዊ የስልጠና ካታሎግ በማሳተም የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ የኢትዮጵያ የሲቪል ሰርቪስ ተቋማት የአቅም ግንባታ ትግበራና የወደፊት አቅጣጫ በሚል ርዕስ ሀገራዊ ወርክሾፕ ተካሂዷል፡፡ Traditional Training አሰጣጥን በCompetency based Training ለመለወጥ ከደንበኛ ተቋማት ጋር አዲስ የስልጠና አሰጣጥና አሠራር ላይ የማስተዋወቅ ስራ ተሰርቷል፡፡ ልዩ ልዩ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በተቋሙ ዌብ ሳይት ላይ እንዲጫኑ በማድረግ ለሰራተኛው ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

የትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥ በመጀመሪያ ድግሪ 9፣ በሁለተኛ ዲግሪ 26 ካሪኩለሞች ክለሳ ተደርጓል፡፡ የ7 አዳዲስ ካሪኩለሞች ቀረጻም ተከናውኗል፡፡ 9,345 የኤሌክትሮኒክስ መጻሕፍትን (በዋጋ ሲተመን ብር 3,105,210.30 የሆነ) ከተለያዩ ዳታቤዞች በማውረድ ከዩኒቨርሲቲው የዲጂታል ሲስተም ሰርቨር ጋር በማገናኘት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተደራሽ ሆነዋል፡ ፡ በደንበኞች ፍላጎት መሰረት 7 አዳዲስ የስልጠናዎች ርዕሶች ተቀርጸው በስልጠና ላይ ሲውሉ 18 የስልጠና ማቴሪያሎችም ተከልሰዋል፡፡ የስልጠና ሞጁል ዝግጅት ጋይድላይን በመጠቀም የስልጠና ሞጁሎች ደረጃቸውን እንዲጠብቁ ተደርጓል፡፡ በዓመቱ 20 ሞጁሎችን ወደ ብቃት-ተኮር ለመቀየር ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 23 ተቀይረዋል፡፡ በስልጠናና ማማከር የISO የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ለማግኘት ብቃትን ከሚያረጋግጥ ድርጅት ጋር ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ ተገብቷል፡ ፡ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በ2012 በዩኒቨርስቲያችን የፕሮግራም ኦዲት ለማድረግ እቅድ ለያዘበት የUrban Enginering ዲፓርትመንትና ለኮሌጁ ማንዋሎችን በመስጠትና ስለአሰራሩ ማብራሪያ በመስጠት ሙያዊ እገዛ ተደርገዋል፡፡ከጥራት ማስጠበቅ ጋር ተያያዥ በሆኑ ርዕሶች ዙሪያ 50 ለሚሆኑ የዲፓርትመንት ተጠሪዎችና ለስልጠናና ማማከር ባለሙያዎች የሙሉ ቀን ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማጠናከርም ከተሰበሰቡ 43 የምርምር ንድፈ ሀሳቦች መካከል 27ቱ የፋይናንስና ፋሲሊቲ ድጋፍ አግኝተው ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ በ2010 አገር አቀፍ ኮንፍረንስ የቀረቡ 24 የምርምር ሥራዎች በፕሮሲዲንግ ታትመው ተሰራጭተዋል፡፡ በ2011 አገር አቀፍ ኮንፈረንስ የቀረቡ የምርምር ስራዎች ከተሳታፊዎች በተገኙ የማዳበሪያ ሀሳቦች መሰረት 22 ምርምሮች በፕሮሲዲንግ ለማሳተም ዝግጁ ተደርጓል፡፡ የምርምር ግብአት ማዕከልም ተደራጅቷል፡፡ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ለመገንበት 22 የተለያዩ ጭብጥ ያላቸው የምርምር ውጤቶች በመምህራንና ተመራማሪዎች የተሰሩ ሲሆን በምርምር ማዕከላትም በሲቪል ሰርቪሱ ላይ ያተኮሩ 4 ምርምሮች ተጠናቀዋል፡፡ በፋይናንስ አስተዳደርና ልማት ኮሌጅ 2 የተለያየዩ ጭብጥ ያላቸው ምርምሮች ተሰርተው የተጠናቀቁ ሲሆን የተመራቂ ተማሪዎች ዳራ ዳሰሳ ጥናት በመስክ መረጃ የማሰባሰብ ስራ በናሙና ከተመረጡት ተቋማት ተሰባስቦ የመረጃ ትንተና ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

አስተዳደራዊ ድጋፍ ስራዎችን ለማጠናከር ከታቀዱ ተግባራት መካከልም በ182 የአስተዳደር መደቦች፣ በአካዳሚክ ዘርፉ ደግሞ የ25 መምህራን ቅጥር ተፈጽሞዋል፡፡ በአስተዳደር ዘርፍ 235 ክፍት የስራ መደብ ለደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ በማውጣት መስፈርቱን ያሟሉ 68 ሠራተኞች የደረጃ ዕድገቱን አግኝተዋል፡ ፡ ለ18 PhD እና ለ5 ማስተርስ በአጠቃላይ ለ23 ሠራተኞችም የማዕረግ ለውጥ ተደርጓል፡፡ የትምህርትና ስልጠና መመሪያ ተሻሽሎና ጸድቆ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን የ1,336 ሠራተኞች መረጃ ወደ ICMIS ሲስተም የማስገባቱ ስራ ተጠናቅቋል፡፡ ለሠራተኞች የIFMIS ሶፍትዌር የመጫን፣ አካውንት የመፍጠር እንዲሁም ቴክኒካል ድጋፍ የማድረግና ለሥልጠና የኮምፒዩተር ላብራቶሪ የማዘጋጀት ሥራ የተከናወነ ሲሆን Office 365 አካውንት የመለየት፣ የማጣራት እንዲሁም ለተጠቃሚዎች አካውንት የመፍጠር ሥራ ተከናውኗል፡፡

በመደበኛ ፍ/ቤት ክርክር ሁለት መዝገቦች ውሳኔ አግኝተው በአንደኛው ላይ ተቋሙ አሸናፊ ሆኖ ብር 350,000.00 በአፈጻጸም ገቢ እንዲደረግ ሲደረግ ብር100,000 ገቢ ለማስደረግ አፈጻጸም ተዘጋጅቷል፡፡ ለግዥ ዳይሬክቶሬት 35 እና ለአካዳሚክ ም/ፕሬዚደንት 4 ውሎች በአጠቃላይ 39 ውሎች እንዲመረመሩ ሲደረግ 25 ጉዳዮች ላይ የህግ አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ ተሰጥቷል፡፡ የመማር ማስተማር፣ የስልጠናና ማማከር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለመደገፍ የህትመትና 251,400 የብዜት ውጤቶችን በስራ ትዕዛዙ መሰረት በሚፈለገው መጠን፤ ጥራትና ጊዜ ለመስራት ተችሏል፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት ፍላጎትን በተመለከተ 13 የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው ግቢዎች

የአሰለጣጠን ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ ለ43 ኮንሰልታንቶች ስልጠና ተሰጥቶ ወደስራ ተገብቷል፡፡ ለ108 ሠራተኞች የህይወት ክህሎት እንዲሁም በሥርዓተ ጾታና በኤች አይቪ/ኤድስ ዙሪያ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በIFMIS፣ ICMIS User Account፣ በሰው ሀብት መረጃ አያያዝና በልሎችም ርዕሶች ለ398 ሰራተኞች እንዲሁም ከጂማ ዩኒቨርሲቲ የCISCO ሥልጠና ክፍል ጋር በመነጋገር የኔትዎርኪንግና የአይሲቲ ኢሴንሻል የአሰልጣኞች ሥልጠና ለአምስት ባለሙያዎች ተሰጥቷል፡፡

ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና መሰረተ ልማትን ለማስፋፋት በዋናው ግቢ አዲስ እየተሰራ ላለው የዲጂታል ላይብራሪ ህንፃ አዲስ ዲዛይን ተዘጋጅቷል፤ ለመምህራንና ልዩ ፍላጎት ላላቸው ወገኖች የሚያገለግል ክፍል የማደራጀት ስራ 75% ተከናውኗል፡፡ የመማሪያ፣ የሰልጣኞች ማደሪያ፣ የስልጠና ክፍሎችና አዳራሾችን ስማርት ለማድረግ በተያዘው ዕቅድ መሰረት የአንድ አዳራሽ የድምጽ ሲስተም፣ ፕሮጀክተር፣ የመብራት ሲስተም፣ የቀለም ስራ እና የምንጣፍ ስራው ተሰርቷል፡፡ የስማርት ክላስ ሩም ለማደራጀትም ለሚያስፈልጉ ዕቃዎች በብር 17,533,445፤ የሰልጣኞች መኝታን እና የስልጠና ክፍሎችን ስማርት ለማድረገግ የሚያስፈልጉ ዕቅዎች በብር 15,251,810 ግዢ ተፈጽሟል፡፡ 10 የስልጠና ክፍሎች ስማርት ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ሲሆን የመኝታ ክፍል ቁሳቁሶችና የካፍቴሪያዎች ወንበርና ጠረጴዛ በአዲስ እንዲቀየሩ ተደርጓል፡፡ ምድረግቢ ማስዋብ /landscaping/ ፕሮጀክቶች ሥራ 85% ለማድረስ ታቅዶ 64.85% ተከናውኗል፡ ፡ በወሊሶና በአዲስ አበባ ለሚገነቡ የካፒታል ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ ለካፒታል ፕሮጀክቶች ብር 180 ሚሊዮን ተመድቦ ስራዎች በተቀመጠላቸው ፕሮግራም መሰረት እየተሰሩና የጊዜ ሰሌዳም በማስቀመጥ አፈጻጸም እየተገመገመ ይገኛል፡፡

ስትራቴጂክ አጋርነትንና ግንኙነትን ለማጠናከር ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጋር ዩኒቨርሲቲው የልህቀት ማዕከል ሆኖ ለማገልገል የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሞ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ከክልሎች፣ ከሴክተር መ/ቤቶችና ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን ነባር አጋርነትና ግንኙነቶችን ተጠናክረዋል፡፡ ከግራዝ (ኦስተሪያ) ዩኒቨርሲቲ፣ ከናይጄሪያ፣ ከእስራኤል እና ከእንግሊዝ አገራት ካሉ የትምህርት ተቋዋማት ጋር ግንኙነት ተፈጥሯል፡፡ ከጉምሩክ ኮሚሽን፤ ከአማራ አመራር ኢንስትትዩት፤ ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል የስልጠና ማእከል፣ ከደቡብ ሱዳን፤ከደቡብ ኮሪያ ሴንትራል ኦፊሻል የስልጠና ኢንስትትዩት፣ ከደቡብ ኮሪያ የሰላም ትምህርት ጋር፣ ከUNDP፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር አጋርነት በመፍጠር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ ከሀንጋሪው Szent Istvan ዩንቨርስቲ አዲስ ዓለም አቀፍ ትምህርታዊ ትስስር የተፈጠረ ሲሆን Uc Leuven- Limburg ከሚባለው የቤልጂየም ዩንቨርሲቲ ጋር አዲስ ዓለም አቀፍ ትስስር ለመፍጠር ውይይት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከSOS London እና ከKehl University (Germany) አዲስ ዓለም አቀፍ ትምህርታዊ ትስስር ተፈጥሯል፡፡ ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሁሉን አቀፍ የጋራ ትብብር ለማድረግ የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሟል፣ Huawe እና Cisco ጋር ግንኙነት ተጀምሯል፡፡

ኮቪድ-19 ተከትሎ ለዩኒቨርስቲው ሠራተኞች የቫይረሱን ስርጭት ለመከላከል እንዲችሉ አስፈላጊውን ግብዓት የሚያሟላና ግንዘቤ የሚያስጨብጥ ኮሚቴ እንዲሁም የግብአት ግዢ አጠቃቀም ተቆጣጣሪ ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሞ እየሠራ ይገኛል፡፡ 1,114,000 ብር በማውጣት ተማሪዎችም ግቢውን በአስቸኳይ ለቀው ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ በዩኒቨርሲቲው በጊዜያዊ ቅጥር ተቀጥረው ይሰሩ ለነበሩ 88 ሰራተኞች የሚሰጡት አገልግሎት በመቋረጡ ለእያንዳንዳቸው ብር 1100 በአጠቃላይ 96800 ወጪ በማድረግ በድጎማ መልክ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በኮሮና ቫይረስ አማካኝነት በችግር ውስጥ የሚገኙ 300 የህብረተሰብ ክፍሎችን ከቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 እና ከየካ ክ/ከተማ ወረዳ 11 በመለየትና ብር 400 ሺህ በመመደብ የዱቄትና ዘይት ልገሳ ተደርጓል፡፡

ዩኒቨርስቲው በለይቶ ማቆያነት በመመረጡ ምክንያት በመጀመሪያው ዙር ለ480 ከውጭ ሃገር ለመጡ ዜጎችንና የተለያዩ ባለሙያዎች በአጠቃላይ 656 ሰዎች፣ በሁለተኛ ዙር ለ394 ኩዋራንታይን የተደረጉ እና ለተለያዩ ባለሙዎች በአጠቃላይ 594 ሰዎች የምግብ እና የመኝታ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ እንግዶች የሠባበሩዋቸውን ንብረቶች በነበረው ሁኔታ ለማስተካከል ብር 143,755.00 ጥሬ እቃዎች አገልግሎት ላይ ሲሆን ዩኒቨርስቲው ከእቅዱ ውጪ ለግብዓት ግዢ ብር 4,298,397.31 ለምግብ 614,687.80 በአጠቃላይ 4,913,085.11 ወጪ በማድረግ አገልገሎቱ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን እንግዶች ባልተጠበቀ ቀን በድንገት በመምጣታቸውና የብዛት ልዩነት በመከሰቱ ከፍተኛ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ ለሰራተኞችና ለጤና ባለሙያዎች ቀደም ብሎ ግንዛቤ ማስጨበጫ ባለመሰጠቱ ከፍተኛ መደናገርና ፍርሀት መፈጠሩ እና መጠለያ ለገቡትም እንግዶች ኦረንቴሽን ያልተሰጣቸው በመሆኑ በተሰጣቸው ክፍል ከመቆየት ይልቅ በየኮሪደሩ በመሰባሰብ አሰራር ላይ ክፍተት ተፈጥሯል፡፡ ከጤና ሚኒስቴር ሆነ ከአደጋና ዝግጁነት እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ቫይረሱን ለመከላከል የሚያገለግሉ ግብዐቶች በወቅቱ አለመድረስ፣ በየብሎኮቹ የተቀመጡትን የመደበኛ ተማሪዎች ንብረቶች ኳራንታይን በገቡ ሰዎች በመሰበሩና የተማሪዎች ንብረቶች ተዘርፈው መወሰድ ካጋጠሙ ችግሮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍም እንደ የመፍትሔ እርምጃዎች ከተወሰዱት መካከል ሠራተኞችን በማስተባበር

መካከል አቋርጦ የሚያልፈው 750ሜ በ100ሜ የወንዝ ዳርቻ ለማልማት በጀት ለማፈላለግ የፕሮጀክት ሰነድ በአረንጓዴ ክለብ ተዘጋጅቶ ለሁለት ተቋማት ተልኮ ምላሹን በመጠበቅ ላይ ይገኛል፡፡ በማህበረሰብ ሬዲዮ ለ1825 ሰዓታት መደበኛ ኘሮግራሞች ለማስተላለፍ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት ሙሉ በሙሉ የተከናወነ ሲሆን የኮረና ወረርሽኝ ወደ ሃገራችን ከገባበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር መደበኛ ፕሮግራሞችን በማጠፍ በሙሉ ስርጭቱ ስለቫይረሱ መረጃ በማድረስ ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስ የሰው ሀይል፣ አሰራር እና አደረጃጀት ለማጎልበት የዩኒቨርሲቲው ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብ ተዘጋጅቶ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና ለዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ የቀረበ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው መዋቅራዊ አደረጃጀትም ከተሰጠው ተልዕኮ ውጤታማነት አንጻር የመፈተሽ ሥራ ተከናውኖ የመጨረሻ ሪፖርት ለዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ቀርቧል፡፡ ለሰራተኞች የትምህርት ዕድል አሰጣጥ መመሪያ ለውይይት በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን የመካከለኛ አመራር ማወዳደሪያ መመሪያ ተዘጋጅቶና ጸድቆ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የተቀናጀ የሠራተኞች መረጃ ሥርዓት /ICMIS/ በመዘርጋት የ1336 ሠራተኞች መረጃ ወደ ሲስተም በመግባቱ ጥያቄዎች በሲስተሙ መሰረት እየተስተናገዱ ይገኛሉ፡፡ የትምህርትና ስልጠና መመሪያ ተሻሽሎና ጸድቆ ተግባራዊ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

የረጅም ጊዜ ትምህርትና አጫጭር ስልጠናዎችን ከመስጠት አንጻር አዳዲስና ነባር ተማሪዎችን በመደበኛ፣ በማታ፣ በክረምትና በእረፍት ቀን ፕሮግራም በአጠቃላይ 7335 (ወ=5557፣ ሴ=1778) ተማሪዎች ተመዝግበው የመማር ማስተማር ሥራው ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ከጎረቤት ሀገሮችም በመጀመሪያ ዲግሪ 24 እና በሁለተኛ ዲግሪ 67 በአጠቃላይ 91 ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛል፡፡ 3932 የጉመሩክ አሰተላላፊዎችን በመመዝገብ የ3570 የመግቢያ ፈተናውን የወሰዱ ተፈታኞችን ውጤት ለሚመለከተው አካል የተላለፈ ሲሆን ከፈተናውም ብር 5,111,600 መሰብሰብ ተችሏል፡፡ ለፐብሊክ ሰርቪስ ተቋማት አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት የሰው ሀይል የመፈጸም አቅምን ለማሻሻል የሚስችሉ ስራዎችን ለመስራት በታቀደው መሰረት ለ50 ተቋማት እና ለ6,426 ሰልጣኞች የስልጠና አገልግሎቱ ሲሰጥ በአንደኛው ዙር ለ458 የጉምሩክ አስተላላፊዎች ስልጠና ተሰጥቷል። 78 የስልጠና ርዕሶች በመከለስና አዳዲስ ስልጠናዎችን በማካተት በ99 ርዕሶች ላይ ስልጠና ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል ፡፡ የፐብሊክ ሰርቪስ ተቋማትን አሰራርና አደረጃጀት ለማሻሻልም ለ6 ደንበኛ ተቋማት የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ ስልጠና ከወሰዱ ተቋማት መካከልም በ22 ተቋማት የክትትል እና ድጋፍ ስራ የተሰራ ሲሆን በ3 ተቋማት ላይ የድህረ ማማከር ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በሀገራችን ሲከሰት ዩኒቨርሲቲው በሶስት ደረጃዎች የሚታዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ የመጀመሪያው የገጽ-ለገጽ የመማር ማስተማሩ ሥራ እንዲቋረጥ በማድረግ የማስተማሪያ ቁሳቁሶች በተለያዩ የኢሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች ለተማሪዎች እንዲደረሱ ተደርጓል፡፡ ከዚያም በማሰከተል ተማሪዎች ግቢውን ለቀው እንዲወጡ ሲወሰን የተማሪዎችን የትራንስፖርት ወጪ በመሸፈን ወደየቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ ቀጣዩና በሶስተኛ ደረጃ ያለውና ተማሪዎች ግቢውን ለቀው ከሄዱ በኋላ በኦንላይን መማር ማስተማር ሂደቱን ለማስቀጠል ያሉትን ተግዳራቶችንና ጥሩ አጋጣሚችን በመለየት የድህረ ምረቃ ተማሪዎች የማስተርስ ቴሲስ ሆነ የኮርስ ወርክ በኦንላይን እንዲቀጥሉ በማድረግ የማጠቃለያ ፈተናና ድፌንስ ተከናውኗል፡፡ የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች የሚያስፈልጉትን የመማሪያ ማቴሪያሎች በኦንላየን እንዲሰጣቸው፤ ተከታታይ ምዘናና ማጠቃለያ ፈተና ግን እንዳይሰጣቸው ተደርጓል፡፡

የሴቶችና ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አካላት ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥም በ2012 የሴት ተማሪዎች አወንታዊ ተሳትፎና ቅበላ እንዲጨምር ሲደረግ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አመቺ የሆኑ የመማሪያ ክፍሎች፣ መመገቢያ ቦታና የመኝታ ስፍራዎች ተመቻችቷል፡፡ ለ13 ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎችም የገንዘብ ድጋፍ ሲደረግ ለ134 ሴት ተማሪዎችና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የኢንፎርሜሽን ሊትሬሲ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሥርዓተ ጾታና ኤችአይቪ/ኤድስ ዙሪያ ለ636 ተማሪዎችና ሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ለ5 አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እና ለ33 ተማሪዎችና ሠራተኞች በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች5 ነጭ ዱላ፣ 3 ቴፕሪከርድ፣ የዊልቸር ጥገናና ለሁለት ተማሪዎች ደግሞ Orthopedic shoe ተሰጥቷል፡፡ በወሊሶ ሥልጠናና ማማከር ማዕከል 80 ስራ የሌላቸዉን እጅ- አጠር እናቶችን ማነሳሳትና ሥራ የመፍጠር ስልጠናና ምክር አገልግሎት ተሰጥቶአል፡፡

የመምህራንና የሰራተኞችን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማሳደግ፣ 27 መምህራን የፒኤች ዲ እንዲሁም 5 የማስተርስ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ለአስተዳደር ሰራተኞች 5 የማስተርስና 2 የመጀመሪያ ድግሪ በነጻ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል፡፡ የተሻለና ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠት በፒኤችዲ 15 እና በማስተር 1 መምህራን ቅጥር ተፈጽሟል፡፡ በአትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት 5 ባለሙያዎች ለአንድ ወር፣ ለ54 የቤተ-መፅሀፍት ሠራተኞች ሰለቤተመፅሐፍት አሰተዳደርና ሊከተሉአቸው ሰለሚገባው ስነምግባር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ብቃት-ተኮር

በኮሚቴው ጥረት በማምሸት ጭምር የተማሪዎችን ንብረቶች ወደ ሌላ ቦታ በማጓጓዝ ለእንግዶች በታውን ማዘጋጀት፣ ለሰራተኞችም ኦረንቴሽን በመስጠት የማነቃቃት ሥራ መሰራቱና የሠራተኞችን እጥረት ለማሟላት የተደረገው ጥረት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ጠንካራ ጎኖች በተመለከተም የታዩ ችግሮች ላይ በውይይት የመፍትሄ ሃሳቦችን ማስቀመጥ መቻሉ፤ ስልጠናዎች ተገልጋዮችን መሰረት በማድረግ ከግቢ ውጪ መስጠት መቻሉ፤ ከስልጠና በፊት፣ በስልጠና ወቅት፣ እና ከስልጠና በኋላ ሰልጣኞችን በፈተና መለየት መቻሉ፤ CBTMን መሰረት ያደረገ የስልጠና ማቴሪያል ዝግጅት መደረጉ እና የCase Files ዝግጅትና የሰልጣኞች ምዘና በመካሄድ ላይ መሆኑ፣ ለሰልጠኞች እና ለስራተኞች የፋሰሊቲ አገልግሎት በተሟላ መልኩ መሰጠት መቻሉ በጠንካራ ጎን የሚወሰዱ ተግባርት ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የቅጥርና የደረጃ እድገት የውስጥ መመሪያ ተዘጋጅቶና ፀድቆ ተግባራዊ መደረጉ፣ የሪሶርስ እጥረትን ለመቅረፍ ሰራተኞቻችን ያላቸውን የፈጠራ ስራ ተጠቅመው ጥገና ማካሄዳቸው ክፍተት ያለባቸዉን የሥራ ድርሻዎችን ሸፍኖ መስራት በጠንካራ ጎን ከተጠቀሱ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ደካማ ጎኖች ከተጠቀሱት መካከልም ከዕቅድ ውጭ የሚመጡ ስራዎች ላይ በማተኮር በዕቅድ የተያዙ ስራዎችን በወቅቱ አለመፈፀም ፣ የድህረ- ሥልጠና ክትትልና ድጋፍ ስራ አናሳ መሆን፣ በመምህራንና ሠራተኞች ላይ የSIMS ክህሎት ችግር መታየት፣ መምህራን በበቂ ሁኔታ በማህበረሰብ ሥራና ጥናታዊ ጽሁፍ ተሳታፊ አለመሆን፣ ለድጅታል ላይብረሪ ክፍሉ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች አለመሟላት፣ የክዋኔ ኦዲት በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት የኦዲት ሽፋን ተደራሽ አለመሆን በበጀት ዓመቱ የታዩ ደካማ ጎኖች ናቸው፡፡

ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ከቤተመጽሀፍቱ ተጠቃሚዎች ብዛት እና ለድጅታል ላይብረሪ ክፍሉ የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች አለመሟላት፣ ለሦስተኛ ዲግሪ ደረጃ ማስተማር የሚችሉ መምህራን በብዛትና በጥራት አለማግኘት፣ የCOVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት የመማር-ማሰተማር ሒደቱ መስተጓጓሉ፣ የአሰልጣኞች ምዘናን የማዘጋጀት አቅምና ክህሎት እጥረት መኖር፣ የወሊሶ ስልጠናና ማማከር ማእከል በወቅቱ ስራ ለማስጀመር የግንባታዎች መጓተት፣ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት በእቅድ የተያዙ ስራዎችን ማከናወን አለመቻሉ በበጀት ዓመቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸው በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎች መምህራን በማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ የሠራተኛውን የሥራ ተነሳሽነት ማሳደግ፣ የሰው ሀይል ፍትሃዊ በሆነ አግባብ አሟጦ መጠቀም፣ በእቅድ መሰረት የስልጠናና የማማከር ስራዎች ላይ ፈጠራን ተላብሶ መስራት፣የተጓደለው የሰው ሃይል ማሟላት፣ የስልጠናና የማማከር አገልግሎቶችን ጥራት አግባብነትና ተደራሽነት ማስፋት፣ የISO ሰርቲፊኬት ለማግኘት ሥራዎችን አጠናክሮ መስራት፣ የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በተዘረጋዉ አሰራር መሰረት መተግበር፣ የዩኒቨርሲቲው የገጽታ ግንባታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት በዩኒቨርሲቲው የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎች ተደርገው መወሰዳቸው በዕቅድ፣ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይርክቶሬት የቀረበው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የ2012 በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያመላክታል፡፡

## International and Public Relations Coordination Directorate

**Contact Address:**
Tel.0116 46 2887,Extension: 253/252/257 , Fax: 0116463016
P.O.Box5648, E-mail: www.lprd @ecsu.edu.et ,
Website: www.ecsu.edu.et, Tweeter: @ECSU tweets ,FM Radio:-100.5MHz
Facebook: Ethiopian Civil Service University




BUILDING CAPACITIES IN PUBLIC SECTOR SINCE 1995

**PRINTED BY** *International & Public Relations Directorate*